


ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ

የስሙ ትርጓሜ ፡ ውክደቱ

- ቁጥሩ ከ4ቱ ወንጌላውያን እና ከ12ቱ ሐዋርያት የሚመደብ ነው።
- የቀድሞ ስሙ ሌዊ ሲሆን ትርጉሙም ሕሩይ /ምርጥ /ማለት ነው። አንድም የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው ።
- ማቴዎስ የሚለውን ስም ያወጣለት መድኃኔዓለም ክርስቶስ ነው ።
- ማቴዎስ ማለት ኅሩይ እመጸብሐን [ከቀራጮች የተመረጠ] ማለት ነው።
- ነገዱ ከነገደ ይሳኮር ሲሆን የአባቱ ስም ዲቁ /እልፍዮስ የእናቱ ስም ካሩትያስ ይባላል ።

ከአገልግሎት መጠሁት

- የተጠራው ቀረጥ ከሚሰበስብበት ሥፍራ ሲሆን ጌታችን ተከተለኝ ሲለው ያለውን ነገር ሁሉ መጽውቶ ተከትሎታል።

- ይህም በብሉይ ልማድ ቅዱስ ኤልሳዕ ቅዱስ ኤልያስን እንደተከተለው..... በዚህም ምክንያት በቁሙ ተስካሩን ያወጣ ሐዋርያ ይባላል ።






ማቴዎስ 9 ፡ 9

“ ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው አየና ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው። በቤቱም በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እነሆ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች መጥተው ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው ተቀመጡ። ''

መጸሕፍት



† ቅዱስ ማቴዎስ 28 ምዕራፍ ያለውን ወንጌል ጽፏል።

† የጻፈው ፍልስጤም ሆኖ ነው/ አንዳንዶችም ፍልስጤም ጀምሮ ምድረ ህንድ ጨርሶታል የሚሉም አሉ።

† ወንጌሉ የተጻፈበት ዘመን ጌታ ባረገ 8/9 ዓመት ማለትም በ41/42 ዓመተ ገደማ እንደተጻፈ ይነገራል።

ምክንያተ ጽሑፍ

- በቃል ያለ ይረሳል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል እንዲሉ አበው ፡ ያስተማራቸውን እንዳይረሱት
- አንድም እንደ አባትነቱ
- አንድም ያላመኑት አይሁድ የአመኑትን ክርስቶስ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም ትላላችሁ ፡ እጅግ ቆጥራችሁ ሰፍራችሁ አሳዩን ብለው ይጠይቋቸው ስለነበር!



አጸጸፍ

- ሎቱ ስብሐት ወአኮቴት 'በዘር በሩካቤ ነው የተጸነሰው' የሚሉ ተነስተው ነበርና እንበለ ዘርዐ ብእሲ በድንግልና ተጸንሶ እንበለ አብ በድንግልና ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ መወለዱን ለማስረዳት!

- 'ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ይበልጠዋል' የሚሉም ነበሩና የክርስቶስ አምላካችን ቅዱስ ዮሐንስ ባርያው/አገልጋዩ መሆኑን ለማስረዳት

- እንዲሁም ከነቢያት አንዱ ነው የሚሉት ነበሩና እግዚአ ነቢያት ፈጣሪ ነቢያት መሆኑን ለማስረዳት



ምሳሌዎች

→ ከ4ቱ ጸወርተ መንበር በገጸ ሰብእ ይመሰላል - ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም እያለ ምድራዊ ልደቱን ይናገራልና!

→ ከአራቱ አፍላጋት በኤፌሶን ይመሰላል [ፈለገ ሐሊብ] ርስትነቱ የሕጻናት ነው - በዘር የሚወለዱ የአበውን ልደት ይጽፋልና

→ ከአራቱ ክፍለ ዘመን በጸደይ ይመሰላል

→ ከአራቱ አንስተ ያዕቆብ በልያ ይመሰላል

ሀገረ ስብከት

- የደረሰችው ሀገረ ስብከት ምድረ ፍልስጤም ናት ::
- ቅዱስ ማቴዎስ ከአምስቱ ዓለማተ መሬት አንዱ በብሔረ ብጹዐን ገብቶ የሰበከ ብቸኛው ሐዋርያ ነው::

- በ40 ዓመተ ምሕረት ገደማ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ አክሱም አከባቢ እንደሰበከ እና አስተምሮ እንዳጠመቃቸው ይነገራል::

  - ፍልስጥኤም,
  - ፋርስ,
  - ባቢሎን,
  - ኢትዮጵያና
  - ዓረቢያ ዞሮ አስተምሯል ::

ተአምር

- ወንጌላዊው በአገልግሎቱ መጨረሻም በትርያ በምትባል አገር ሲያስተምር አገረ ገዥው አሠረው። በወህኒ ቤቱም ጌታው ለንግድ የሰጠውን ገንዘብ ማዕበል ወስዶበት በዕዳ ምክንያት የሚያለቅስ አንድ እሥረኛ አገኘና አጽናንቶ መኰነኑ ገንዘቡን ከሕዝቡ ለምኖ እንዲከፍለው በመሻት ከእሥር እንደሚፈታው ከባሕር ዳርቻም የወደቀ ወርቅ የተሞላ ከረጢት እንደሚያገኝ ያንንም ለጌታው ከሰጠ በኋላ ከዕዳና ከእስር ነጻ እንደሚሆን አስረዳው።

- ሰውየውም ቅዱስ ማቴዎስ የተናገረው ሁሉ ስለ ተፈጸመለት "በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ" ለቅዱስ ማቴዎስ እየሰገደ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመኑን ተናገረ ደስታውን ገለጸ።

- በዚያ ይህንን ተዓምር ሲያዩ ብዙዎች አምነዋል።

ሰማዕትነት

- በዚህም ምክንያት አርያኖስ በሚባል ንጉሥ ትዕዛዝ ጥቅምት 12ቀን ሰማዕትነት ተቀብሏል።
- አንዳንዶችም ብስባራ በምትባል ሥፍራ ሰማዕትነት እንደተቀበለ ይነገራሉ [ትር. ወንጌል]!



ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ

ቅዱስ ያዕቆብ

† ቁጥሩ ከ 12ቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ሲሆን በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል [ምዕራፍ 10]

† 'መንግስተ ሰማያት ቀርባለች' ብለው እንዲሰበኩ ድውዮችን እንዲ ፈውሱ : ሙታንን እንዲያነሱ : ለምጻሞችን እንዲያነጹ : አጋንንትን እንዲያወጡ:: እንዲሁ የተቀበሉትን እንዲሁ እንዲሰጡ አልጫ የሆነችውን ዓለም በወንጌል ጨውነት እንዲያጣፍጡ ልባቸው በክህደት የጨለመባቸውን በጸጋ በተሰጣቸው ብርሃንነት ለዓለም እንዲያበሩ ሐዋርያዊ አገልግሎትን እንዲያገለግሉ ከተላኩት ቁጥሩ ከ12ቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ነው::

† #Dar ያዕቆብ ማለት አሃዜ ሰኮና ማለት ነው [ዘፍ.....]

ሀገረ ስብከት

- ቅዱስ ያዕቆብ በዚያው በኢየሩሳሌም የክርስቶስ የአምላካችንን የማዳን ሥራ ከጽንሰት እስከ ልደት ከስቅለት እስከ እርገት አስተምሮ እንዲሁም በእጁ ገቢረ ተዓምራትን አድርጎ ቡዙዎቹን ወደ አሚነ ሥላሴ አምጥቷል ::

ሰማዕትነት

- በወንጌል እንዴተጻፈ ነቢይ በገዛ ሃገሩ አይከበርም እንዴተባለ በዚህም በእነርሱ ላይ ያደረ በቅንዐት እንድነሱበት አድርጎ በቀላውድዎስ ቄሳር በዛው በኢየሩሳሌም በድንጋይ ቀጥቅጠው ሰማዕትነት እንዲቀበል አድርገዋል።



ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ

ዉልደት እና እድገቱ

- ትውልዱ ከነገደ ዮሴፍ ሲሆን ቁጥሩ ከ12ቱ ቅዱሳን ሐዋርያት ነው ከላይ ቅድም እንዳልነው የዓለም ብርሃን የዓለም ጨው ከተባሉት ቅዱሳን አበው አንዱ ነው ::

- የአባቱ ስም ያዕቆብ ነው ::



የስሙ ትርጓሜ

† ታዴዎስ ማለት :- ልብድ ሰሪ አሳ ወጋሪ ማለት ነው። የአሳ ማጥመጃ ይሰራ ነበርና!

† አንድም ዘር ወማእረር ማለት ነው (ዘር እና መከር ማለት ነው)ኦሪትን እንዴ ዘር ወንጌልን እንዴ መከር አድርጎ አስተምሯልና እንዲሁም በቀጣይ እንደምናየው ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ሆኖ ባለው ታሪክ ዕለቱኑ ዘርቶ ለመሥዋዕት አድርሷልና ።

† አንድም ልበ ድዮስ - ካህነ አምላክ ማለት ነው ።

† ቅዱስ ታዴዎስ ሌላኛው ስሙ ይሁዳ ነው - ’’ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳም’’ (ሐዋርያት 1÷13)

† 'የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ ጌታ ሆይ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው አለው።’ [ዮሐንስ 14:22]

ሀገረ ስብከት

† ቅዱሳን ሐዋርያት ለስብከተ ወንጌል እጣ ሲጣጣሉ ለእርሱ ሶርያ ደርሳዋለች ::

† ከዚያ በተጨማሪ :

- በፍልስጤም
- በአርመን
- በፋርስ ዞሮ አስተምሯል ::

ተዐምር

ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር ያደረጉት ተዐምር

- ግመል በመርፌ ቀዳዳ አሳልፏል።



ሰማዕትነት

† እረፍቱ ሐምሌ 2 ነው!




የ12ቱ ሐዋርያት አማሚት
ቅ.ጴጥሮስ
ተገልብጦ ተሰቀለ
ቅ.እንድርያስ
በ X ምልክት ተሰቀለ
የዘዘዴዎስ ልጅ ቅ.ያዕቆብ
በድንጋይ እና በጎራዴ
ወንጌላዊው ቅ.ዮሐንስ
በመሰደድ
ቅ.በርተሎሜዎስ
በመሰቀል, ቆዳ መገፈፍ እና አንገት በመቀላት
ቅ.ፊሊጶስ
ተዘቅዝቆ በመሰቀል
ቅ.ቶማስ
በጦር በመወጋት
የአልፍዮስ ልጅ ቅ.ያዕቆብ
በመሰቀል
ወንጌላዊው ቅ.ማቴዎስ
በመቃጠል
የጌታ ወንድም ቅ.ይሁዳ
በመሰቀል እና በጦር መወጋት
ቅ.ስምዖን
በመሰቀል
ቅ.ማትያስ
በመወገር

ዝክረ ሐዋርያት

ዝክረ ሐዋርያት ለምን?

† ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ በዘመኑ ስለ ነበሩት የፈረስ ግልብያ [ስፖርት ነክ ነገሮች] የሥልጣኔ ጫፍ አድርገው ለሚያስቡ ክርስቲያኖች ሲናገር ፡



'ከእነዚህ ከአንዳንዶቹ ስለ ቅዱስ ኢሳያስ, ቅዱስ ኤርምያስ, ቅዱስ ሕዝቅኤል ቅዱስ አሞጽ ወይም የቅዱሳን ነቢያት የቅዱሳን ሐዋርያት ቁጥራቸው ስንት ነው ብለህ ብትጠየቃቸው ድዳ ይመስል ዝም ይላሉ አንደበታቸው ይተሳሰራል የሚናገሩት ነገር ያጣሉ:: ነገር ግን ስለ ፈረሶቻቸው ስለ ተሸቀዳደሚዎቹ ወይም ስለ ሌሎች ስፖርት ነክ ቢጠየቁ ጋዜጠኛ ጥርት ልቅም አድርጎ ከሚያቀርበው ዜና ይልቅ በስሜት እና በኃይል ሆነው ስለ እስፖርቱ ትንታኔ ማስረዳት ይችላሉ!'

ዝክረ ሐዋርያት ለምን?

- ይህ በዚያ ዘመን የነበሩትን በራድ ወይም ትኩስ ያልሆኑትን አስቸጋሪ ክርስቲያኖች ብቻ የሚነካ ሳይሆን አሁን ባለንበት ዘመን ከቅድስት ቤተክርስቲያን ማኅፀን በጥምቀት ተወልደን በዚያው ውስጥ ያለን ነገር ያለመለምን ያላበብን ያላፈራን እድገትን ያላሳየን እንደውም ዝም ብለን ቀጭጨን የቀረን መዓዛ ቅዱሳን የሌለን ቡዙዎቻችንን የሚያካትት ነው ::

- በሥም ክርስቲያን ነገር ግን ሁለት ጡቶቿን ጠብተን አድገን [ብሉይ እና ሐዲስን] ምግቧን እየበላን /ቅዱሳት መጽሐፍትን እናታችንን [ቅድስት ቤተክርስቲያንን] : ቤተሰቦቻችንን [ቅዱሳንን] የማናውቅ ጥቂት የምንባል አይደለንም:: በእርግጥ በተደጋጋሚ ስማቸው ሲነሳ ገድላቸውም ተደጋግሞ ሲነገር አንዳንዴም ስማቸው ከደማችን ጋ የተዋሐደ እስኪመስለን ድረስ ከአፋችን የማንለያቸው ቅዱሳን አሉ :: ነገር ግን ብርኃን ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው "በቅዱሳን ሐዋርያትና በቅዱሳን ነቢያት መሠረት ላይ የታነጽን እኛ ወደ ማዕዘኑ ራስ ድንጋይ መድረሻ ድልድያችንን ሳናውቅ ጫፉን ለመያዝ እንዴት እንሮጣለን?!

ዝክረ ሐዋርያት ለምን?

- ሰማዕቷ ቅድስት አርሴማን እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን የማያውቅ ክርስቲያን የለም ፡ ሐዋርያትን ግን ይህንን ያክል ሥፍራ ሰጥተን አናውቃቸውም።

- ይህንን ስል እኒህን የመሰሉ ምድራውያን መልዐክ ማወቁ መልካም አይደለም እያልኩ አይደለም ። መጀመሪያ ማወቅ ያለብንም እነርሱን ነበር ። በወንጌል ከአንዱ ኮከብ የአንዱ ኮከር ይበልጣል እንደተባለ የቅዱሳን ሐዋርያት ክብር እጅጉን ከሌሎች ቅዱሳን ሁሉ ይበልጣል።

✥ አባቶቻችንን እንወቅ!!!

አባቱን የማያውቅ እንዲሉ አበው መሰረቶቻችንን እንወቃቸው!

➵ አንድም ክብራቸውን የምንገልጠው ስለ እነርሱ በመማር የምናውቀውን ለሰው በማካፈል [ዜና ህይወታቸውን በመጨዋወት] በምልጃቸው በመመካት እነርሱን ለመምሰል በመጣር ነውና እንወቃቸው ::

➵ እንደውስ በዘወትር ጸሎታችን ላይ ሐዋርያት በሰሯት በአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን እናምናለን አይደል የምንለው " እና ማኅደረ መለኮት የሆነችውን ቅድስት ቤተክርስቲያንን የሰሩልንን አባቶቻችን እንደምን ለመማር ለማወቅ አንጓጓም ?!

"በጌታችን አምነን እጅግ ደስ ይበለን እምነታችን እንደ ሐዋርያት እምነት ነውና!"

[ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ አቡሊድስ ምዕራፍ ፶፱÷፮]

ስብሐት እእዛዘአብሔር!